Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**ጥር 27 ቀን 2017 ዓ.ም.**

**<u>በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲያስገቡ ለማሳሰብ የወጣው ይፋዊ መግለጫ ዝርዝር</u>**

ይህ ይፋዊ መግለጫ ኩባንያዎቹ በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ እና ኢንዱስትሪ ሳይገደብ ከአምሳ (50) በላይ የአክስዮን ባለቤቶች ያሏቸው (በህዝብ ባለቤትነት የተያዙ) እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ አክስዮኖችን ለህዝብ ሽያጭ በማቅረብ ከህዝብ ገንዘብን የሚሰበስቡ ኩባንያዎችን ይመለከታል።

ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2024 (“መመሪያ”) ከህዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ስራ ላይ መዋሉ ይታወሳል። የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን (“ባለስልጣን”) ለኢንቨስተር ከለላ የመስጠት እንዲሁም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማውጣት እና የግብይት ስራ ስርዓትን የተከተለ፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽነት በሰፈነበት ሁኔታ የሚካሄድበትን የተሟላ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳርን ለመፍጠር የተነሳበትን አላማ ከግብ ለማድረስ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና ሽያጩን የሚቆጣጠር የህግ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል።

**የይፋዊ መግለጫው አላማ**

መመሪያው ከሚያስተዋውቀው አዲስ የቁጥጥር ስርዓት ጋር ተያይዞ ይህ ይፋዊ መግለጫ ለቁጥጥር ሂደቱ የሚረዱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያለመ ነው። በዚህም መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች ነባር አክስዮኖቻቸውን ቁጥጥር ወደ የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለማምጣት ስለአክስዮኖቹ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን።

በዚህ መልኩ የሚሰበሰበው መረጃም በገበያው ውስጥ ጠንካራ መረጃ ይፋ የሚደረግበት እና ግልጽነት የተሞላበት የገበያ አሰራር እንዲፈጠር የሚያግዝ በመሆኑ በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች እስከ መጋቢት 1 ቀን 2017 ዓ.ም. የሚከተሉትን መረጃዎች ለባለስልጣኑ እንዲያቀርቡ እናሳስባለን።

1. በሙሉ የተከፈሉ እና ቃል የተገባባቸው አስክስዮኖችን ጨምሮ ጠቅላላ የአክስዮን ብዛት፣
2. የባለአክስዮኖቹን ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም በባለአክስዮኑ የተያዘው የአክስዮን ብዛትን የሚያካትት የባለአክስዮኖች ዝርዝር፣
3. አክስዮኖቹ ከወጡበት ቀን አንስቶ ያለው የነባር አክስዮኖች ዋጋ፣
4. የሁሉም ነባር አክስዮኖች የወጡበት ወይም ለሽያጭ የቀረቡበት የሽያጭ ጊዜ መጀመሪያ እና መጠናቀቅያ፣
5. የአክስዮን ሽያጭ ጥሪውን ለማቅረብ ጥቅም ላይ የዋለ የሽያጭ ማቅረብያ ሰነድ ኮፒ፣
6. ሽያጩን አስመልክቶ የቀረበ ማስታወቅያ ይዘትና የቀረበበት የሚዲያ አማራጭ እንዲሁም
7. ለነባርም ሆነ አዲስ ባለአክስዮኖች የቀረበ ማንኛውም ያልተጠናቀቀ ለህዝብ የቀረበ የአክስዮኖች ሽያጭ አክስዮኖቹ እንዲውጡ የተፈቀደበት የባለአክስዮኖች ቃለ-ጉባኤን እንዲሁም ሌሎች ከአክስዮኑ መውጣት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችን አካተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ።

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**የመረጃው አቀራረብ**

የመረጃው አቅራቢ ኩባንያው አስተዳደሮች የሚቀርቡትን ሰንዶች የያዘ መግለጫ ላይ በመፈረም የቀረቡት ሰነዶችና መረጃዎች ትክክለኛ እና የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ማመልከቻዎቹ:-

- በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክ/ከተማ በሚገኘው የባለስልጣኑ ዋና መስርያ ቤት ምናዩ ህንጻ 17ተኛ ፎቅ በወረቀት መቅረብ አለበት።
- የሰነዶቹ ቅጂ በ lgizachew@ecma.gov.et እንዲሁም smohammed@ecma.gov.et የኢሜል አድራሻ መላክ አለባቸው።

**አስፈላጊ መረጃ**

በተቀመጠው የጊዜ ገድብ ውስጥ ከላይ የተጠየቁትን መረጃዎች የማያቀርቡ ኩባንያዎች ማንኛውም አይነት የአክስዮን አቅርቦታቸው ከህዳር 5 በኋላ እንደቀረበ ተደርጎ ይወሰዳል።

**ማሳሰብያ**

***ነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች:-*** ***በዚህ ይፋዊ መግለጫ መሰረት የሚቀርብ መረጃ የነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በባልስልጣኑ እንደማስመዝገብ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም።*** በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች የመመሪያውን የምዝገባ መስፈርቶች በማሟላት ከህዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም. አንስቶ በሚቆጠረው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል።

**ያልተጠናቀቁ ሽያጮች:-** በተጨማሪም መመሪያው ስራ ላይ ከዋለበት ቀን አስቀድመው ሽያጫቸው ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከህዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም. አንስቶ በሚቆጠረው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መመዝገብ እንደሚገባቸው ይደነግጋል።

**አዲስ ሽያጭ**:- እባኮትን ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለሽያጭ ከመቅረቡ አስቀድሞ መመዝገብ እንዳለበት ልብ ይበሉ። በዚህም መሰረት አዲስ ሽያጭ ማካሄድ የሚፈልጉ ኩባንያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸውን አስቀድመው በባለስልጣኑ ያስመዝግቡ።

እነዚህን የምዝገባ መስፈርቶች አለማሟላት በአዋጁ እና በመመሪያው መሰረት ቅጣትን ያስከትላል።

ስለዚህም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኩባንያዎች በሙሉ ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ወደ የሚደረግበት የካፒታል ገበያ የሚደረገውን ሽግግር ያግዝ ዘንድ እነዚህን መስፈርቶች እንዲያከብሩ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን

ጥር 27 ቀን 2017 ዓ.ም.